# የቅንጅት የድጋፍ ማኅበር በስዊድን

# CUD-SWEDEN STÖD FÖRENING I SVERIGE

## የትግል ፍሬ ፈገግታን ሲያላብሰ

የትግል ፍሬ አብቦና ደምቆ በመላው ሐገራችን ሲታይና ኢትዮጵያዊያንን ሁሉ በደስታ ስሜት እየኮረኮረ ፈገግታን ሲያላብሰ ማየት ምንኛ ያስደስታል?

በሐገርም ሆነ በውጭ የምንኖር ኢትዮጵያውያን ይህ የአበባ ጊዜ ወደ ፍሪያማነት የሚቀየርበትን ጊዜ ለማየት በጉጉት እንጠባበቃለን::ከእስር ከተፈቱት መሪዎቻችን ጎን ሆነንም ለሐገራችን ብሩህ ተስፋ አዝሎ የተነሳውን የቅንጂትን ዓላማ ለማስፈጸም ከመቸውም የበለጠ እንደምንሰራ ቃል እንገባለን::

የቅንጂት መሪዎች ለሰው ልጆች መብት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ግነባታ የከፈሉት መስዋዕትነት ወደፊት ሐገራችን ከምትኮራበት የታሪክ ክስተቶች አንዱ እንደሚሆን እርግጠኞች ነን:: ምክንያቱም የቅንጂት መሪዎች ዘረኝነትን ያጠፋና ኢትዮጵዊነትን ያደሰ የህዝባዊ ንቅናቄ መሪዎች በመሆናቸው ነው:: እነዚህ ቆራጥ መሪዎች ያሳዩት ያመራር ብቃት የዓላማ ጽናትና የሐገራችን ሕዝቦች ለዚህ ሰላማዊ ትግል በደማቸው የከፈሉት መስዋእትነት ለሐገራችን ብቻ ሳይሆን በጨቁዋኝ ስርዓት ውስጥ ላሉ ሕዝቦች ሁሉ ትምህርት የሚሆን ታላቅ ምሳሌ ነው:: በአንድነት ተነስቶ ለዓላማ የሚደረግን ሕዝባዊ ንቅናቄንም የሚገታ ኃይል እንደማይገኝ ያረጋገጠ ሃቅ ነው::

ቅንጂት ያነሳው የህዝብን ስሜት ያካተተ ፕሮግራም ነው:: ለዚህ ነው ቅንጂት መንፈስ ነው የምንለው:: (በኢትዮጵያ ህዝብ ውስጥ ያለ መንፈስ)
የኢትጵያ ሕዝብ በዚህ የትግል ሂደት አንባገነኖችን የማይሸከም ለመብቱ የሚታገል በመልከም አስተዳደር በወንድማማችነት በእህትማማችነት የሚኖርና በአንድነቱ የጸና ሕዝብ መሆኑንን አረጋግጡዋል::

የቅንጂት የድጋፍ ማኅበር በስዊድን በመሪዎቻችንን መፈታት የተሰማውን ደስታ ለመሪዎቻችንና ለቤተሰቦቻቸው እየገለጠ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኩዋን ደስ አለን ይላል:: በስልጣን ላይ ያለው መንግሥትም የህዝብን ጥያቄ እንዲያከብር ለሐገራችን እድገት የሚበጀውን የሕግ የበላይነትን ተቀብሎ እውነተኛ እርቀ ሰላም እንዲደረግና ሕዝብን ያሳተፈ የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ እንዲደረግ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ሃላፊነት እንዳለበት ያሳስባል::

የቅንጂት የድጋፍ ማኅበር በስዊድን ሕዝባችን የጀመረው የዲሞክራሲዊ ስርዓት ግንባታ መስመር ይዞ እንዲቀጥል ያልተቆጠበ ድጋፍ እንደሚደርግ ያረጋግጣል:: ለቅነጂት መሪዎች ያለውን አክብሮትና ለቀጣዩም ትግል አብሮዋቸው እንደሚቆም ይገልጻል::

### የቅንጂት የድጋፍ ማኅበር በስዊድን